Patients' Bill of Rights – Amharic

የታካሚዎች መሰረታዊ መብቶች መግለጫ ሰነድ

ለታካሚዎች የሚሆን ምጥን ማጣቀሻ መጽሐፍ

የሕጉ ዓላማ፦ የሕግ አውጭው አካል ዓላማ እና የዚህ መግለጫ ፍላጎት የጤና እንክብካቤ መሰጫ ተቋማትን ታካሚዎች ጥቅምና ደህንነት ለማሰጠበቅ ነው። የትኛውም የጤና እንክብካቤ ተቋም አንድን ታካሚ ወደ ተቋሙ ለማሰገባት እነዚህን መብቶች እንዲተው እንደ ሁኔታ ሊጠብቅበት አይገባም። ማንኛውም የታካሚ ሞግዚት ወይም ተንከባካቢ ወይም፣ ሞግዚት ወይም ተንከባካቢ በማይኖርበት ጊዜ፣ ፍላጎት ያለው ሰው፣ ለታካሚው ጥቅም እነዚህን መብቶች ለማሰከበር ሊፈልግ ይችላል። በአሰተዳደራዊ ኤጀንሲዎች ወይም በኑዛዜ/ውርስ ህጋዊነት ማረጋገጫ ፍ/ቤት ወይም የመጠበቅ ወይም የተንከባካቢነት ሰልጣን ያለው፣ የካውንቲ ፍ/ቤት እማኳኝነት ሞግዚት ወይም ተንከባካቢ ያለው፣ ፍላጎት ያለው ሰው ለታካሚው ጥቅም እነዚህን መብቶች ለማሰከበር ሊፈልግ ይችላል። የሕግ የችሎት ሂደት ውጤት ማሰፈጸሚያን በመጠባበቅ ላይ ሆኖ የጤና እጠባበቅ ተቋሙ በቅን ልቦና፣ የሞግዚትን ወይም ተንከባካቢን መመሪያ ማክበር ይችላል። የዚህ ክፍል ዓላማ እያንዳንዱ ታካሚ የሲቪል እና የሃይማኖት ነፃነት፣ በተናጠል የግል ውሳኔዎችን የማሳለፍ እና የሚገኙትን እማራጮች የማወቅ መብትን ጨምሮ የማይጣስ እና ተቋሙ የእነዚህን መብቶች ሙሉ በሙሉ በተግባር ላይ ለማዋል የሚያበረታታ እና የሚያግዝ መሆኑን ነው።

ትርጓሜዎች፦ ለዚህ መግለጫ ዓላማ፣ "ታካሚ" ማለት ለዚያ ሰው እካላዊ ወይም እእምሯዊ ጤንነት ላይ ተመርምሮ ለሚደረግ ምርመራ ወይም ህክምና ዓላማው ለተከታታይ ጊዜ ከ 24 ሰዓታት በላይ ቆይታ ተኝቶ በሚታከምበት ተቋም ለከባድ የጤና እንክብካቤ የሚድን ሰው ነው። "ታካሚ" ደግሞ ለኣቅመ መጠን ያልደረሰ በሚኒሶታ ሕግ 1986፣ ምእራፍ 326፣ በክፍል 7 በተደነገገው መሠረት ለመኖሪያ መርሃ ግብር የገባ ልጅ ማለት ነው። ለዚህ መግለጫ ዓላማ "ታካሚ" ማለት ደግሞ የእእምሮ ጤንነት ሕክምናን በተመላላሽ ታካሚነት ወይም በማህበረሰብ ድጋፍ መርሃ ግብር ወይም በሌላ የማህበረሰብ-ተኮር መርሃ ግብር የሚቀበል ማንኛውም ሰው ነው።

የህዝብ ፖሊሲ መግለጫ፦ የዚህ ግዛት የህዝብ ፖሊሲ ሆኖ የታወጀ የእያንዳንዱ ታካሚ ጥቅም በታካሚዎች መሰረታዊ መብቶች እዋጅ፣ በዚህ መግለጫ ውሰጥ የተገለጹ መብቶችን የሚያጠቃልል ነገር ግን በዚያ ብቻ ያልተገደቡ መብቶች የተጠበቁ ናቸው።

1. ሰለ መብቶች መረጃ

ታካሚዎች፣ በቅበላ ጊዜ በሕክምና ተቋሙ ውሰጥ በሚቆዩበት ጊዜ ወይም በሕብረተሰቡ ውሰጥ ሕክምና እና ቆይታ ወቅት ለእነርሱ ጥበቃ የሕግ መብቶች እንዳላቸው ሊነገራቸው ይገባል እና እነዚህም በዚህ ክፍል ውሰጥ በሚመለከታቸው መብቶችና ግዴታዎች የተቀመጠ የጽሑፍ መግለጫ ውሰጥ ተገልጸዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ በክፍል 7 በተደነገገው መሠረት ለመኖሪያ መርሃ-ግብር የገቡ ታካሚዎች ፣ በጽሑፍ የተሰጠው መግለጫ በተጨማሪ በክፍል 253B.04 ንዑሰ እንቀጽ 2 በተደነገገው መሠረት ዕድሜያቸው 16 እና ከዚያ በላይ የሆነ ሰው መለቀቅ የመጠየቅ መብት ይገልጻል እንዲሁም በመኖሪያ መርሃ ግብሮች ውሰጥ ላሉ ታካሚዎች ጠበቃ እና የሕግ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች። ግለሰቦችን እና የድርጅት ሰሞችን እና የሰልክ ቁጥሮችን መዘርዝር አለባቸው።

የግንኙነት እክል ላለባቸው እና ከእንግሊዝኛ ውጭ ሌላ ቋንቋ ለሚናገሩ ሰዎች ተመጣጣኝ መሰተንግዶ መዘጋጀት አለበት። የወቅቱ መገልገያዎች ፖሊሲዎች፣ የግዛት እና የአካባቢ የጤና ባለሥልጣናት ምርመራ ግኝቶች፣ እና በጽሑፍ የሰፈረው የመብቶች መግለጫ ተጨማሪ ማብራሪያ ለታካሚዎች፣ ለሞግዚቶቻቸው ወይም እነርሱ ለመረጡት ተወካዮቻቸው ለአሰተዳዳሪው ወይም ለሌላ ለተሰየመ ሠራተኛ፣ በምእራፍ 13፣ የውሂብ ልምዶች ህግ፣ እና ክፍል 626.557፣ ተጋላጭ ለሆኑ እዋቂዎችን የሚመለከት በተጠየቀ ጊዜ እንዲያገኙት ያሰፈልጋል።

2. ትሑት እያያዝ

ታካሚዎች በግላዊነትቻው በጤና ጥበቃ ተቋም ውሰጥ አገልግሎት በሚሰጡ ሠራተኞች ወይም ተቀጣሪዎች በትህትና እና እክብሮት የመያዝ መብት አላቸው።

3. ተገቢ የጤና እንክብካቤ

በግለሰቦች ፍላጎቶች ላይ በመመርኮዝ ታካሚዎች ተገቢውን የሕክምና እና የግል እንክብካቤ የማግኘት መብት አላቸው። ይህ መብት አገልግሎቱ በህዝባዊ ወይም በግል ሀብቶች የማይመለሰ በሚሆንበት ቦታ የተገደበ ነው።

4. የሐኪም ማንነት

ታካሚዎች የእነርሱን እንክብካቤ ማስተባበር ሀላፊነት ያለው ሀኪም ስም፣ የንግድ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥር እና ልዩ ሙያ ካለው በጽሑፍ ሊኖራቸው ወይም ሊሰጣቸው ይገባል። በታካሚው እንክብካቤ መዝገብ ውስጥ ባለው በሚከታተለው ሀኪም እንደተቀመጠው፣ በህክምና አስራር የማይመከር በሚሆንበት ጊዜ መረጃው ለታካሚው ሞግዚት ወይም በታካሚው የእርሱ ወይም የእርሷ ተወካይ ለተሰየመው ሌላ ሰው መረጃው መሰጠት አለበት።

5. ከሌሎች የጤና አገልግሎቶች ጋር ያለው ግንኙነት

ከውጭ አቅራቢ አገልግሎቶችን የሚቀበሉ ታካሚዎች እንደጠየቁ የአቅራቢው ማንነት ሊነገራቸው ይችላል። መረጃው የውጪውን አቅራቢ ሰም፣ አድራሻውን እና ሊሰጠው የሚችለውን አገልግሎት መግለጫ ማካተት አለበት። በታካሚው እንክብካቤ መዝገብ ውስጥ ባለው በሚከታተለው ሀኪም እንደተቀመጠው፣ በህክምና አስራር የማይመከር በሚሆንበት ጊዜ መረጃው ለታካሚው ሞግዚት ወይም በታካሚው የእርሱ ወይም የእርሷ ተወካይ ለተሰየመው ሌላ ሰው መረጃው መሰጠት አለበት።

6. ሰለ ሕክምና መረጃ

ታካሚዎች የእነርሱን ምርመራ፣ ሕክምና፣ እማራጮች፣ ሰጋቶች እና የወደፊት-ሁኔታን በሚመለከት በሐኪሞቻቸው አማካይነት የተሟላ እና የወቅቱን መረጃ እንዲገልጽ ሀኪሙ ሕጋዊ ግዴታ በሚጠብቅበት ይሰጣቸዋል። ይህ መረጃ ታካሚዎች በተግባራዊ ሁኔታ እንዲረዱ በሚጠበቅባቸው ቃላትና ቋንቋ መሆን አለበት። ታካሚዎች ከቤተሰብ አባል ወይም ከሌላ የተመረጠ ተወካይ ወይም ከሁለቱም ጋር አብሮ መሆን ይችላሉ። ይህ መረጃ የህክምና ወይም ዋና የህክምና የሰነ-ልቦና ውጤቶችን እና አማራጮቹን ማካተት አለበት። በታካሚው እንክብካቤ መዝገብ ውስጥ ባለው በሚከታተለው ሀኪም እንደተቀመጠው፣ በህክምና አስራር የማይመከር በሚሆንበት ጊዜ መረጃው ለታካሚው ሞግዚት ወይም በታካሚው የእርሱ ወይም የእርሷ ተወካይ ለተሰየመው ሌላ ሰው መረጃው መሰጠት አለበት። ግለሰቦች ይህንን መረጃ ያለመቀበል መብት አላቸው።

በማንኛውም የጡት ካንሰር ዓይነት የሚሠቃይ ታካሚ አሰቀድሞ ወይም ቅበላ እንደተደረገለት ወይም ሕክምናው በሚሰጥበት ጊዜ እና በሚቆዩበት ጊዜ ሁሉ የቀዶ ጥገና፣ የጨረር ሕክምና፣ ወይም የኬሞቴራፒ ሕክምናዎች፣ ወይም የሕክምናዎቹ ጥምረት እና ከእነዚያ የእያንዳንዱ ዘዴ ጋር የተዛመዱ አደጋዎችን ጨምሮ ህክምና ባለሙያው ሊያውቅ ከሚችሉት ሁሉም ውጤታማ የሕክምና ዘዴዎች ሁሉ ሙሉ በሙሉ እንዲያውቅ ይደረጋል።

7. ህክምና ለቤተሰብ አባላት የማሳወቅ ዕቅድ በማቀድ ውስጥ ተሳትፎ፦

(a) ታካሚዎች በጤና እንክብካቤ እቅዳቸው ውስጥ የመሳተፍ መብት አላቸው። ይህ መብት ሕክምና እና አማራጮች ላይ ከግለሰብ እንክብካቤ ሰጪዎች ጋር የመወያየት እድልን፣ በመደበኛ እንክብካቤ ሰብሰባዎች የመጠየቅ እና የመሳተፍ እድል እንዲሁም የቤተሰብ አባል ወይም ሌላ የተመረጠ ተወካይ ወይም ሁለቱንም የማካተት መብት ይጨምራል። ታካሚው መገኘት በማይችልበት ሁኔታ አንድ የቤተሰብ አባል ወይም በታካሚው የተመረጠው ሌላ ተወካይ በእነዚያ ሰብሰባዎች ውስጥ መካተት ይችላል። የተመረጠው ተወካይ የታካሚውን ምርጫ አጋር ሊያካትት ይችላል።

(b) ወደ ተቋሙ የገባ አንድ ታካሚ እራሱን የሳተ ሰመመን ውስጥ ወይም መግባባት የማይችል ከሆነ፣ በአንቀጽ (ሐ) እንደተፈለገው ተቋሙ ለቤተሰብ ወይም ወደ ተቋሙ የገባው ታካሚ በድንገተኛ አደጋ ጊዜ ተጠሪ ሰው አድርጎ ታካሚው በጽሑፍ የተሰየመው ሰው አባል ለማሳወቅ ተገቢ ጥረቶችን ማድረግ አለበት። ተቋሙ የሚያውቀው ወይም የሚያምንበት ምክንያት ታካሚው በተቃራኒው ውጤታማ የቅድሚያ መመሪያ ካለው ወይም ታካሚው በሕክምና ዕቅድ ውስጥ የቤተሰብ አባል መካተትን እንደማይፈልጉ በጽሑፍ ካልገለጹ በስተቀር ተቋሙ የቤተሰቡ አባል በሕክምና ዕቅድ ውስጥ እንዲሳተፍ መፍቀድ አለበት። የቤተሰብ አባልን ካሳወቁ በኋላ ግን አንድ የቤተሰብ አባል በሕክምና ዕቅድ ውስጥ እንዲሳተፍ ከመፍቀድዎ በፊት፣ የታካሚው የጤና እንክብካቤ ውሳኔዎች ጋር በተያያዘ ታካሚው የቅድሚያ መመሪያን እንደፈፀመ ለማወቅ፣ተቋሙ ምክንያታዊ የሕክምና ልምድን መሠረት በማድረግ ተገቢ ጥረቶችን ማድረግ አለበት። ለዚህ አንቀጽ ዓላማ “ምክንያታዊ ጥረቶች” የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

(1) የታካሚውን የግል ንብረቶችን መመርመር፤

(2) በተቋሙ የተያዙ የታካሚውን የሕክምና መዝገቦችን መመርመር፤

(3) ማንኛውንም የድንገተኛ አደጋ ተጠሪ ወይም የቤተሰብ አባል ሲያነጋግሩ ታካሚው የቅድሚያ መመሪያ እንደፈፀመ እና ታካሚው በተለምዶ የሚንከባከበው ሀኪም ካለው፤ እና ታካሚው የቅድመ መመሪያን ያከናውን ከነበረ ታካሚው በተንከባካቢነት የሚሄድበትን

(4) ሀኪም መጠየቅ፣ ከታወቀ፣ ታካሚው በተለምዶ የሚንከባከበው ሀኪም ካለው።ታካሚው የቅድመ መመሪያን ያከናውን ከነበረ ታካሚው በተንከባካቢነት የሚሄድበትን ሀኪም መጠየቅ፣ ከታወቀ፣ ታካሚው በተለምዶ የሚንከባከበው ሀኪም ካለው። ተቋሙ የቤተሰብ አባልን ወይም የድንገተኛ አደጋ ተጠሪን የሚያሳውቅ ከሆነ ወይም አንድ የቤተሰብ አባል በዚህ አንቀጽ መሠረት ሕክምናውን በማቀድ ውስጥ እንዲሳተፍ ከፈቀደ፣ ተቋሙ የቤተሰብ አባል ወይም የአደጋ ጊዜ ተጠሪ ወይም የቤተሰቡ አባል ተሳትፎ ተገቢ ያልሆነ ወይም የታካሚውን የግለሰቦችን የግል መብት የሚጥስ በመሆኑ ምክንያት ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂ አይሆንም።

(c) የቤተሰብን አባል ወይም የተሰየመን የአደጋ ጊዜ ተጠሪ ለማሳወቅ ምክንያታዊ ጥረት ሲያደርግ ተቋሙ የቤተሰብ አባሎቹን ለመለየት መሞከር አለበት ወይም የታካሚውን የግል ንብረቶች እና በተቋሙ የተያዙ የታካሚውን የሕክምና መዝገቦችን መመርመር። ተቋሙ ከቤተሰቡ አባል ወይም ከተሰየመ የድንገተኛ አደጋ ጊዜ ተጠሪ ጋር ቅበላ ከተደረገ በኋላ በሰዓታት ውስጥ ማሳወቅ ካልቻለ፣ ተቋሙ ታካሚው መቀበሉን እና ተቋሙ ቤተሰብን ወይም የተሰየመ የድንገተኛ ጊዜ ተጠሪ ማሳወቅ አለመቻሉን ለካውንቲው ማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲ ወይም ለአከባቢው የሕግ አስከባሪ ኤጄንሲ ያሳውቃል። የካውንቲው ማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲ እና የአካባቢ ህግ አስከባሪ ኤጀንሲው የቤተሰብ አባልን ወይም የተሰየመ የድንገተኛ ጊዜ ተጠሪ ለመለየት እና ለማሳወቅ ይረዳል። አንድ ተቋም የሚያግዝ የካውንቲው ማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲ ወይም የአካባቢ የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲ በማሳወቅ መሰረት ለሚፈጠር ጉዳት ወይም የቤተሰቡ አባል ተገቢ ያልሆነ ወይም የታካሚውን የግለሰቦችን መብት ጥሰት ለታካሚው ተጠያቂ አይሆንም።

8. የእንክብካቤ ቀጣይነት

የተቋሙ ፖሊሲ በሚፈቅደው መሠረት ታካሚዎች በተሰተካከለ መደበኛ እና የሰራተኞች ምደባ ቀጣይነት እንክብካቤ እንዲደረግላቸው መብት አላቸው።

9. እንክብካቤን ያለመቀበል መብት

ብቃት ያላቸው ታካሚዎች መብት ቁጥር 6 ላይ በተጠቀሰው መረጃ መሠረት ህክምናን ያለመቀበል መብት አላቸው። ታካሚው ሁኔታዎችን መረዳት በማይችልበት ሁኔታ ግን ብቃት የለውም ተብሎ ካልተረጋገጠ ወይም የህግ መሰፈርቶች ህክምናን ያለመቀበል መብትን በሚገድቡበት ጊዜ ሁኔታዎችና አጠቃላይ ሁነቶች በታካሚው የህክምና መዝገብ ውስጥ በሚከታተለው ህኪም ሙሉ በሙሉ ይመዘገባሉ።

10. ሳይንሳዊ የሙከራ ምርምር

ታካሚው በሙከራ ምርምር ውስጥ ከመሳተፉ በፊት በጽሑፍ የተጻፈ መረዳት የታከለበት የፈቃድ ሰምምነት መገኘት አለበት። ታካሚዎች ተሳትፎን ያለመቀበል መብት አላቸው። ሁለቱም ሰምምነት እና እምቢታ በግል እንክብካቤ መዝገብ ውስጥ ይመዘገባሉ።

11. ከማጎሳቆል ነፃ መሆን

በተጋላጭ የጎልማሶች ጥበቃ ሕግ ውስጥ በተገለፀው መሠረት ታካሚዎች ከሚደርሰባቸው ጥቃት ነፃ ይሆናሉ። “ማጎሳቆል” ማለት በክፍል 626.5572፣ ንዑስ ክፍል 15፣ ወይም ሆን ብሎ እና ህክምናዊ ያልሆነ አካላዊ ሥቃይን ወይም ጉዳት ማድረግ ወይም ማንኛውም እእምሯዊ ወይም ሰሜታዊ ጭንቀትን ለማምጣት የታሰበ የማያቋርጥ አካሄድ ነው። በጽሑፍ ለተወሰነ እና ለተወሰነ ጊዜ በታካሚዎች ሐኪም ከተመረመረ በኋላ እናም ታካሚውን እራሱን ከሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ወይም እንዳይጎዳ ለመከላከል አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ። ከተፈቀደለት በስተቀር ለህክምና ያልሆነ ኬሚካል እና አካላዊ ገደቦች ነፃ መሆን አለበት።

12. የሕክምና ግላዊነት

ታካሚዎች ከህክምና እና ከግል እንክብካቤ መርሃ ግብሮች ጋር በተያያዘ የእክብሮት እና የግላዊነት መብት አላቸው። የጉዳይ ውይይት፣ ምክክር፣ ምርመራ እና ሕክምና በሚሰጥራዊነት እና በጥንቃቄ ይከናወናል። ለታካሚ ደህንነት ወይም ለድጋፍ አሰፈላጊ ካልሆነ በስተቀር የግለሰቦችን በመጸዳጃ ቤት፣ በመታጠብ እና በሌሎች የግል ንፅህና እንቅስቃሴዎች ወቅት ግላዊነት መከበር አለበት።

13. የመዝገቦች ምሰጢራዊነት

ታካሚዎች የግል እና የህክምና መዝገቦቻቸውን በሚሰጥር መያዝ የተረጋገጠላቸው ከመሆናቸውም በላይ ከተቋሙ ውጭ ለሌላ ማንኛውም ሰው ነፃ ለመልቀቅ መፍቀድ ወይም ያለመፍቀድ ይችላሉ። ከመዝገቦች የመዝገቦች ቅጂዎች እና የጽሑፍ መረጃዎች በዚህ ንዑስ እንቀጽ እና በክፍል 144.292 መሠረት መገኘት ይኖርባቸዋል። ይህ መብት በጤና ጥበቃ መምሪያ የቅሬታ ምርመራዎች እና ግምገማዎች፣ በሦስተኛ ወገን የክፍያ ኮንትራቶች በሚፈለግበት ወይም በሕግ የቀረበ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

14. የሚገኝ የአገልግሎት ይፋ ማድረግ

ታካሚዎች በሚቀበሉበት ወይም በሚቆዩበት ጊዜ እና በመኖሪያው ጊዜ ውስጥ በቋሚነት ወይም በየቀኑ የመኝታ ክፍል ዋጋ ውስጥ የተካተቱ አገልግሎቶችን እና ሌሎች አገልግሎቶች በተጨማሪ ክፍያዎች የሚገኙ መሆናቸውን ይነገራቸዋል። ቀደም ሲል ለተዘረዘሩት አገልግሎቶች ወይም Medicare ወይም የሕክምና እገዛ መርሃ ግብር ለማንኛውም ወይም ለሁሉም የሚከፍል መሆኑን ወይም አለመሆኑን የሚመለከቱ መረጃዎችን ታካሚዎች እንዲያገኙ ለመርዳት ጥረት ያደርጋሉ።

15. ምላሽ ሰጪ አገልግሎት

ታካሚዎች ለጥያቄዎቻቸው እና ለጥየቃዎቻቸው ፈጣን እና ምክንያታዊ ምላሽ የማግኘት መብት አላቸው።

16. የግል ግላዊነት

ታካሚዎች ከማህበራዊ፣ ከሃይማኖታዊ እና ከስነ-ልቦና ደህንነት ጋር በተያያዘ የግላዊነታቸውን፣ የግለሰባዊ እና ባህላዊ ማንነታቸውን ግምት ውስጥ የማስገባት መብት አላቸው።

17. ቅሬታዎች

እንደ ታካሚዎች እና ዜጎች መብቶቻቸውን እንዲረዱ እና እንዲጠቀሙባቸው በሕክምና ተቋሙ ውስጥ በቆዩበት ጊዜ ሁሉ ይበረታታሉ እንዲሁም ይታገዛሉ። ታካሚዎች ቅሬታዎችን የማስማት እና የማስወጣት ሰጋትን ጨምሮ ለተቋሙ ሠራተኞች እና ለመረጡት ሌሎች ፖሊሲዎች እና አገልግሎቶች ሰለሚደረጉ ለውጦች ሊመክሩት ይችላሉ፣ ከጫና፣ ጣልቃገብነት፣ ማሸማቀቅ፣ ወይም ብቀላ የማስውጣት

ዛቻን ጨምሮ ነጻ ናቸው። የጤና ተቋም አቤቱታዎች ጽ/ቤት እንዲሁም አድራሻዎች እና የሰልክ ቁጥሮች እና በአረጋዊ አሜሪካኖች ሕግ (ክፍል) 307(ሀ)(12) መሠረት በአከባቢው የቤት እንክብካቤ የሚደረግላቸው እንባ ጠባቂ ሚሰጥራዊ በሆነ ቦታ ላይ ይለጠፋሉ።

በክፍል 7 እንደተገለፀው እያንዳንዱ አጣዳፊ እንክብካቤ የተኛቶ ታካሚ ሕክምና ተቋም፣ እያንዳንዱ የመኖሪያ መርሃግብር እንዲሁም የተመላላሽ ታካሚ የአእምሮ ጤና አገልግሎቶችን የሚሰጡ ከሁለት ሰዎች በላይ የሚጠቀም እያንዳንዱ ተቋም ቢያንሰ በጥብቅ የሚከተለው የሂደት ቅሬታ ያለው የጽሑፍ ውሰጣዊ ቅሬታ አሰራር ይኖረዋል፣ ለተቋማት ምላሽ መሰጫ የጊዜ ገደቦችን ጨምሮ የጊዜ ገደቦችን ይገልጻል፣ የታካሚው ጠበቃ ድጋፍ እንዲኖረው ያደርጋል፣ ለጽሑፍ ቅሬታዎች በጽሑፍ ምላሽ ይጠይቃል፤ እና ቅሬታው ያልተፈታ እንደሆነ ገለልተኛ ውሳኔ ሰጪ ጊዜውን የጠበቀ ውሳኔ ይሰጣል። በክፍል 7 እንደተገለፀው በሆሰፒታሎች ላይ የተመሠረተ የመጀመሪያ ህክምና መርሃ ግብሮች እና የተመላላሽ ታካሚዎች የቀዶ ጥገና ማእከሎች 144.691 እና በክፍል 62D.11 ጋር በጤና እንክብካቤ ድርጅቶች ተገዢነት በጽሑፍ ለቀረበ የውሰጥ ቅሬታ አሰራር ሂደት መሰፈርቶች ተገዢ ናቸው።

18. የግንኙነት ግላዊነት

ታካሚዎች ከሚመርጡት ሰው ጋር ግንኙነት መፍጠር እና በግል መግባባት እና በሚኒሶታ ኮሚትመንት አክት እሰካልተሰጠ ድረስ፣ ወደ ተቋሙ መግባት እና ለቀው መውጣት ይችላሉ። ታካሚዎች በራሳቸው ወጪ የመፃፊያ መሣሪያዎች፣ ጽህፈት መሳሪያ እና ፖስታ ሊኖራችው ይችላል። በሕክምና ወይም በኤሌክትሮኒክ መሳሪያ የማይመከር እና ና በሐኪሙ የህክምና መዝገብ ውሰጥ የሰፈረ ካልሆነ በሰተቀር የግል ደብዳቤ ያለ ጣልቃ ገብነት ይላካል እና ሳይከፈት ይቀበላሉ። ታካሚዎች ጥሪዎችን ማድረግና መቀበል እንዲሁም በግል ማውራት የሚችሉበት ሰልክ ማግኘት አለባቸው። የግል ሰፍራ መሰጠት የማይችሉ ተቋማት የታካሚዎችን ጥሪዎች ግላዊነት ለማሰጠበቅ ምክንያታዊ የሆነ መሰናዶን ማድረግ ኣለበቸው። ይህ መብት በሕክምና ባለሙያው በታካሚ የሕክምና መዝገብ ውሰጥ በሰፈረው መሠረት በሕክምና ሊታሰብ በማይችልበት ቦታ የተገደበ ነው። በተጋላጭ የጎልማሶች ጥበቃ ሕግ መሠረት በፕሮግራም የተገደበ በሚሆንበት ጊዜ በክፍል 626.557፣ ንዑስ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 2 አንቀጽ 2 ላይ እንደተጠቀሰው ይህ መብት በዚህ ውሰን መሆን አለበት።

19. የግል ንብረት

ታካሚዎች የግል ልብሳቸውን እና ንብረቶቻቸውን ቦታ እንደፈቀደ መያዝ እና መጠቀም ይችላሉ፣ ይህን ማድረግ የሌሎችን ታካሚዎች መብት የሚጥሰ ካልሆነ በሰተቀር፣ እንዲሁም በሕክምና ወይም በተመዘገበ የህክምና፣ ደህንነት የመርሃግብር ተፈጥሮ ምክንያቶች በመርሃ ግብር የማይመከር ካልሆነ በሰተቀር። ተቋሙ ለጠፉ ወይም ለተሰረቁ እቃዎች ካሳ ሊያቀርብ ይችላል፣ ግን አይጠበቅበትም።

20. ለተቋም አገልግሎቶች

እነዚህ ተግባራት ለሕክምና ዓላማዎች እና በግላዊ የሕክምና መዝገብ ውሰጥ በተገቢው ግብ ጋር የተዛመዱ ናቸው ተብለው ካልተካተቱ በሰተቀር ታካሚዎች ለተቋም የጉልበት ሥራ ወይም አገልግሎት ማከናዎን የለባቸውም።

21. የጥበቃ እና የመሟገት አገልግሎቶች

በዚህ ክፍል ውሰጥ እና በሌላ ህግ የተዘረዘሩትን መብቶች መረዳትን፣ ማሰከበርን እና ጥበቃን ማግኘት እንዲችል ታካሚዎች በማንኛውም የሚገኙ የመብቶች ጥበቃ አገልግሎቶች እና የመከራከሪያ አገልግሎቶች ውሰጥ ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ የማግኘት መብት አላቸው። ይህ መብት በታካሚው እና በግል መብቶች ጥበቃ አገልግሎት ወኪል ወይም በተሟጋች አገልግሎት ተወካይ መካከል የግል የሕሳብ ልውውጥን እድል ይጨምራል።

22. የግንኙነት መረጃ የመለዋወጥ እና የመተባበር መብት

የፌዴራል ሕግ ያልተፈቀደ የታካሚ መለያዎችን መረጃ ለደዋዮች እና ለጎብኝዎች እንዳይገለጽ በሚከለክልበት ተቋም ውሰጥ ከገቡ በኋላ ከታካሚው ጋር ለመገናኘት ለሚፈልጉ ደዋዮች እና ጎብኝዎች በሕክምና ተቋሙ መገኘቱን ለመግለጽ እድሉን፣ ለታካሚው ወይም የየሕግ ሞግዚቱ ወይም የታካሚው ተንከባካቢ መሰጠት አለበት። በተቻለ መጠን የታካሚው የሕግ ሞግዚት ወይም ተንከባካቢ የታካሚውን በተቋሙ ውሰጥ መገኘት ይፋ ማድረግን በተመለከተ የታካሚውን አሰተያየት ግምት ውሰጥ ማሰገባት ይኖርበታል።

ታካሚው በምዕራፍ 145ሐ መሠረት በታካሚው የጤና እንክብካቤ ወኪል ሆኖ የሾመው ግለሰብ የመጎብኘት መብት አለው እና በአንቀጽ 22 ሰር በታካሚው በተሰየመው ግለሰብ የመጎብኘት እና የጤና እንክብካቤ ውሳኔ የማድረግ መብት አለው።

ወደ ተቋሙ ሲገባ፣ ታካሚው፣ ወይም የታካሚው የሕግ ሞግዚት ወይም የታካሚው ተንከባካቢ ጉብኝትን እና የጤና እንክብካቤ ውሳኔን በተመለከተ ዝምድና የሌለው የታካሚው የቅርብ ወዳጅ ቦታን የሚይዝ ሰው እንዲሰይሙ እድል ሊሰጣቸው ይገባል። በታካሚው የጤና መዝገብ ውሰጥ ሰያሜ መካተት አለበት። የጤና እንክብካቤ ውሳኔን በሚመለከት በዚህ አንቀጽ ሰር በተሰየመው ይልቅ በ 145C መሠረት የጤና እንክብካቤ መመሪያ ወይም የጤና እንክብካቤ ወኪል የሚደረግ ምደባ ይሠራል። እንዲሁም ዝምድና የሌለው ሰው ደግሞ በታካሚው ወይም በታካሚው ቤተሰብ ሊለይ ይችላል።

በኬሚካል ጥገኛ ወይም በአእምሮ ህመም ለታመሙ ሕፃናት ወይም በሰሜት ለተረበሹ ለአካለ መጠን ያልደረሱ

ሕፃናት አገልግሎት በ 24 ሰዓት መሠረት የሚሰጡ የመኖሪያ መርሃግብሮች ውሰጥ ተጨማሪ መብቶች፦

23. መነጠል እና ገደቦች

በክፍል 7 እንደተገለፀው ወደ መኖሪያ መርሃ ግብር የተቀበለው ለአካለ መጠን ያልደረሰ ታካሚ፣ ታካሚው በራሱ ወይም በሌሎች ላይ አካላዊ ጉዳት የማድረስ እድሉ ከሚፈጠር የአደጋ ጊዜ ሁኔታ ውሰጥ ካልሆነ በስተቀር ከአካላዊ ቁጥጥር እና መነጠል ነጻ የመሆን መብት አለው። እነዚህ የአሰራር ሂደቶች ለሰነ-ሰርዓት ዓላማዎች፣ የመርሃ-ግብር ህጎችን ለማስከበር፣ ወይም ለሠራተኞች ምቾት ተብሎ ጥቅም ላይ ላይውሉ ይችላሉ። ገለልተኛ በእነሰተኛ ገዳቢ የሆኑ እርምጃዎች ውጤታማ ወይም የማያዋጡ በሚሆኑበት እና ለአጭር ጊዜ አሰፈላጊ ከሆነ ብቻ ከሀኪም፣ ሳይካትሪስት፣ ወይም ፍቃድ ያለው የሰነ-ልቦና ባለሙያ ኣሰቀድሞ ፈቃድ ሲሰጥ ብቻ መነጠል ወይም ገደብ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።

24. የሕክምና ዕቅድ

በክፍል 7 እንደተገለፀው ወደ መኖሪያ መርሃግብር የገባ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ታካሚ በባህሪያቸው ጉዳዮች የጉዳተኛውን ችግሮች፣ የዕቅዱ ትክክለኛ ግቦችን እና ለአካለ መጠን ያልደረሰ ታካሚ ተኝቶ ህክምና የሚያሰፈልገው የጊዜ ርዝመት ለመቀነሰ የሚጠቀሙበትን የአሰራር ሂደቶች የሚያብራራ የጽሑፍ የህክምና እቅድ መብት አለው። እቅዱ በተጨማሪም ተገቢ ከሆነው አነሰተኛ ቁጥጥር ላለው ተቋም ለመልቀቅ ግቦችን መግለጽ እና ተገቢ ከሆነ የክትትል ህክምና እርምጃዎች እና አገልግሎቶች ይገልጻል። በተቻለ መጠን ለአካለ መጠን ያልደረሰ ታካሚ እና ወላጆቹ ወይም አሳዳጊዎች በሕክምና እና የማሰወጫ ዕቅድ ማዘጋጀት ውሰጥ መሳተፍ አለባቸው።

የፌዴራል መብቶች

እ.ኤ.አ. ከጁላይ 2 ቀን 1999 ጀምሮ የፌዴራል ታካሚዎች መብቶች s ህግ (42(42 CFR ክፍል 482) ሥራ ላይ ውሏል። የመብቶች sማሰታወቂያዎችን በሚመለከቱበት ጊዜ ታካሚዎች በፌዴራል ሕጎች መሠረት የተሰጧቸው መብቶች አሏቸው። የእሱ/ እሷን እንክብካቤ በተመለከተ የመብቶች ማሰከበር፣ ግላዊነት እና ደህንነት፤ የእሱ/የእሷ መዛግብት ምሰጢራዊነት፤ በከባድ ህክምና እና የቀዶ ጥገና አገልግሎት ለመሰጠት በህክምናው የሚያሰፈልግ ካልሆነ በስተቀር ከመለየት፣ እና በባህሪ አስተዳደር ጥቅም ላይ ከሚውል በህክምናው የሚያሰፈልግ ካልሆነ በስተቀር ከገደብ ነፃ መሆን። ቅሬታዎችን ወይም ጭንቀቶችን ለማሰመዝገብ የሚረዱ ቅደም ተከተሎችን በተመለከተ በዚህ ጽሑፍ የመጨረሻ ገጽ ላይ ይገኛል።

በፌዴራል ሕግ 42 CFR §482.13 ውሰጥ ያሉ መብቶች የተሳትፎ ሁኔታ፦ የታካሚዎች መብቶች። አንድ ሆሰፒታል እያንዳንዱ የታካሚውን መብቶች መጠበቅ እና ማሰተዋወቅ አለበት።

(a) መደበኛ፦ የመብቶች ማሳወቂያ።

(1) **አንድ ሆሰፒታል ለእያንዳንዱ ታካሚ ወይም አሰፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የታካሚውን ተወካይ (በግዛቱ ህግ መሰረት እንደተፈቀደለት)፣ የታካሚውን እንክብካቤ ከማቅረቡ ወይም ከማቋረጡ አሰቀድሞ ማሳወቅ አለበት።**

(2) ሆሰፒታሉ የታካሚ ቅሬታዎች አፋጣኝ መፍትሔ የመፈለግ ሂደት ማቋቋም አለበት፣ እንዲሁም ቅሬታ ለማቅረብ ማንን ማነጋገር እንዳለበት ለእያንዳንዱ ታካሚ ማሳወቅ አለበት። የሆሰፒታሉ የበላይ አካል የቅሬታ ማቅረቢያውን ሂደት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማሰፈፀም እና ኃላፊነት የሚሰማው መሆን አለበት እንዲሁም ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በጽሑፍ ካልወከለ በቀር ቅሬታዎችን መመርመር እና መፍታት አለበት። የቅሬታ ማቅረቢያው ሂደት ተገቢውን የእንክብካቤ ጥራት ወይም ያለጊዜው መውጣቱ አግባብ ላለው የአጠቃቀም እና የጥራት ቁጥጥር አቻ ግምገማ ድርጅት የታካሚ ሰጋቶችን ወዲያውኑ የሚያሰተላልፍበትን ዘዴ ማካተት አለበት። በትንሹ፦

(i) የታካሚውን የጽሑፍ ወይም የቃል ቅሬታ ለሆሰፒታል ለማሰገባት ሆሰፒታሉ ግልፅ የሆነ የአሠራር ሂደት መመሰረት አለበት።

(ii) የቅሬታ ማቅረቢያ ሂደት ቅሬታውን እና ምላሽ የመሰጫ የጊዜ ገደቦችን መወሰን አለበት።

(iii) ቅሬታውን በሚፈታበት ጊዜ ሆሰፒታሉ የታካሚውን የሆሰፒታሉ ተጠሪ ግለሰብ ሰም የያዘ፣ ታካሚውን በመወከል ቅሬታውን ለማጣራት የተወሰዱ እርምጃዎች፣ የቅሬታ ሂደት ውጤትና የእርሱን ውሳኔ እና የተጠናቀቀበት ቀን በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።

(b) መደበኛ፦ መብቶችን ተግባራዊ ማድረግ።

(1) ታካሚው በእራሱ እንክብካቤ እቅድ ዝግጅትና ትግበራ ውሰጥ የመሳተፍ መብት አለው።

(2) ታካሚው ወይም የእርሱ ተወካይ (በግዛቱ ሕግ እንደተፈቀደለት) እንክብካቤውን በተመለከተ በእውቀት ላይ የተመሠረተ ውሳኔ የማድረግ መብት አለው። የታካሚው መብቶች ሰለ ጤናው ሁኔታ መታወቅን፣ በእንክብካቤ እቅድ እና ህክምና ውሰጥ መሳተፍ እና ህክምናን መጠየቅ ወይም አለመቀበልን ያጠቃልላል። ይህ መብት በሕክምና አላሰፈላጊ ወይም ተገቢ ያልሆነ ተደርገው የሚታዩትን የህክምና አቅርቦቶች ወይም አገልግሎቶችን ለማቅረብ የሚጠይቅ ዘዴ ሆኖ መታየት የለበትም።

(3) ታካሚው የቅድሚያ መመሪያዎችን የመቅረጽ እንዲሁም በሆሰፒታሉ ውሰጥ እንክብካቤ የሚያደርጉ የሆሰፒታል ሰራተኞች እና ባለሙያዎች በዚህ መመሪያ(48) መሠረት በዚህ መመሪያ (መመሪያ) መሠረት ተገዢነትን እና በ §489.የዚህ ክፍል መሰረት (ፍቺ)፣ §489. የዚህ ክፍል (ለኣቅራቢዎች የሚጠበቅባቸው)፣ §489.የከዚህ ክፍል (ተግባራዊ የሚሆኑበት ቀናት) የማግኘት መብት አለው።

(4) ታካሚው/ዋ የመረጡትን የቤተሰብ አባል ወይም ተወካይ የማግኘት ወይም የእሱን/የሷን የግል ሀኪም ወደ ሆስፒታል መግባቷን ወዲያውኑ ለሐኪሙ የማሳወቅ መብት አላቸው።

(c) መደበኛ፦ ግላዊነት እና ደህንነት።

(1) ታካሚው የራሱ ግላዊነት መብት አለው።

(2) ታካሚው ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንክብካቤ የማግኘት መብት አለው።

(3) ታካሚው ከማንኛውም ዓይነት በደል ወይም ትንኮሳ ነፃ የመሆን መብት አለው።

(d) መደበኛ፦ የታካሚ ሪኮርዶች ምስጢራዊነት።

(1) ታካሚው የክሊኒካዊ መዝገቦቹን ምስጢራዊነት የማግኘት መብት አለው።

(2) ታካሚው በተገቢው የጊዜ ገደብ ውስጥ ክሊኒካዊ መዝገቦቹ ውስጥ የተካተቱ መረጃዎችን የማግኘት መብት አለው። ሆስፒታሉ ግለሰቦች የራሳቸውን የህክምና መዛግብት ለማግኘት የሚያደርጉትን ህጋዊ ጥረቶችን እንዳያደናቅፍ እና መዝገብ አያያዝ ሰርዓት በሚፈቅደው መሰረት እነዚህን ጥያቄዎች በፍጥነት ለማሟላት መትጋት ይኖርበታል።

(e) መደበኛ፦ እገዳ ወይም መነጠል። ሁሉም ታካሚዎች ከአካላዊ ወይም ከአእምሯዊ በደል እና ከአካላዊ ቅጣት ነፃ የመሆን መብት አላቸው። ሁሉም ታካሚዎች በግዳጅ፣ በሰነሰርዓት፣ በማመቻቸት፣ ወይም በሰራተኞች በቀል ለመበቀል፣ ከማንኛውም ዓይነት መታገድ ወይም ከመነጠል ነፃ የመሆን መብት አላቸው። እገዳ ወይም መነጠል የታካሚውን፣ የሰራተኛውን ወይም የሌሎችን የቅርብ አካላዊ ደኅንነት ለመጠበቅ ብቻ እንዲተገበር የሚያሰገድድ ሲሆን በሚቻልበት ጊዜ በተቻለ ፍጥነት መቋረጥ አለበት።

(1) ትርጓሜዎች።

(i) እገዳው-

(A) የታካሚው እጆቹን፣ እግሮቹን፣ አካሉን ወይም ጭንቅላቱን በነፃነት የመንቀሳቀስ ችሎታን የሚያዳክም ወይም የሚቀንስ ማንኛውም ማንዋል ዘዴ፣ አካላዊ ወይም ሜካኒካል መሳሪያ፣ ቁሳቁስ ወይም መሳሪያ፤ ወይም

(B) እንድ የታመመ ሰው ባህሪን ለመቆጣጠር ወይም የታካሚውን የመንቀሳቀስ ነጻነት ለመገደብ እንደ መታገድ ሆኖ ሲያገለግል እና የታካሚውን ሁኔታ መደበኛ ህክምና ወይም የመድኃኒት መጠን አይደለም።

(C) የእግድ መቆጣጠሪያ እንደ ኦርቶፔዲክስ የታዘዙ መሳሪያዎችን፣ የቀዶ ጥገና የቁስል ማሸጎችን፣ ወይም ማስሪያዎችን፣ የመከላከያ ሄልሜቶችን ወይም የተለመዱ አካላዊ ምርመራዎችን ለማድረግ ወይም ታካሚው ከአልጋ ላይ እንዳይወድቅ ለመከላከል፣ ኖርበት በተለያዩ ተግባራት ውስጥ እንዲሳተፍ ለማስቻል አስፈላጊ የሆኑ የታካሚ አካላዊ መያዝ ሁኔታን የሚመለከቱ ሌሎች ዘዴዎችን አይጨምርም (ይህ አካላዊ እጀባን አይጨምርም)።

(ii) መነጠል ታካሚው ለብቻው በክፍል ውስጥ ወይም ቦታ የግዴታ እንዲቆይ ማድረግ ወይም ከመሄድ የታገደበት ነው። መነጠል ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው ለጥቃት ወይም ራስን የማጥፋት ባህሪን ለመቆጣጠር ብቻ ነው።

(2) (ገደብ ወይም መነጠል ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉት አነስተኛውን ውስን ጣልቃ ገብነት የታካሚውን የሰራተኛ አባል ወይም ሌሎችን ከአደጋ ለመጠበቅ ውጤታማ አለመሆናቸው ሲወሰኑ ብቻ ነው።

(3) ጥቅም ላይ የሚውለው የመገደብ ወይም የመነጠል ቴክኒክ ገዳቢነቱ በጣም አናሳ የሆነና ታካሚውን፣ ሰራተኛውን ወይም ሌሎች ሰዎችን ከጉዳት ለመጠበቅ ውጤታማ የሆነው ነው።

(4) የእግድ ወይም መነጠል አጠቃቀም መሆን ያለበት -

(i) በታካሚው የእንክብካቤ እቅድ በጽሑፍ ማሻሻያ መሠረት፤ እና

(ii) በግዛቱ ሕግ መሠረት በሆስፒታል ፖሊሲ በሚወሰነው በአሰተማማኝ እና በተገቢው የእግድ እና መነጠል ቴክኒኮች መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል።

(5) የእገዳው ወይም የመነጠሉ አጠቃቀሙ በህኪም ትእዛዝ ወይም በሕግ የተፈቀደለት ገለልተኛ ባለሞያ በ § 482.12(ሐ) እንደተገለፀው እና በሆስፒታሉ መመሪያ ውስጥ ከግዛት ሕግ ጋር እገዳን ወይም መነጠልን ለማዘዝ ሰልጣን የተሰጠው ህኪም ትዕዛዝ መሆን አለበት።

(6) የእግዳ ወይም መነጠል ትእዛዝ ለመጠቀም ትዕዛዞች በጭራሽ እንደ ማቆሚያ ቅደም ተከተል ወይም እንደአሰፈላጊነቱ (PRN) መፃፍ የለባቸውም።

(7) የሚከታተለው ሐኪም ገደቡን ወይም መነጠሉን ካላዘዘ በተቻለ ፍጥነት የሚከታተለውን ሐኪም ማማከር አለበት።

(8) ይበልጥ ገዳቢ በሆነው የግዛት ሕግ ካልተደነገገ በስተቀር -

(i) የታካሚውን፣ የሰራተኛውን ወይም የሌላኛውን አካላዊ ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ሁከት ወይም ራስን የማጥፋት ባህሪ ለማስተዳደር የሚያገለግል እያንዳንዱ ትእዛዝ ወይም መታገድ በሚቀጥሉት አስከ 24 ሰዓታት ድረስ በሚከተሉት ገደቦች ብቻ ይታደሳል።

(A) ዕድሜያቸው 18 ዓመት ለሆኑ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ አዋቂዎች 4 ሰዓታት፤

(B) ዕድሜያቸው ከ 9 እስከ 17 ዓመት ለሆኑ ታዳጊዎች 2 ሰዓታት፤ ወይም

(C) ዕድሜያቸው ከ 9 ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት 1 ሰዓት፤ እና

(ii) በእመፅ ወይም በራሰ ላይ ጉዳት የማድረስ ባህሪን ለማሰተዳደር አዲሰ ትእዛዝ ከመጻፍዎ በፊት ከ 24 ሰዓታት በኋላ፣ በ § 482.12 እንደተጠቀሰው ለታካሚው እንክብካቤ ሃላፊነት ያለው ሀኪም ወይም ሌላ ፍቃድ ያለው ገለልተኛ ባለሙያ በክልል ሕግ መሠረት በዚህ የሆሰፒታል ፖሊሲ ውሰጥ እገዳን ወይም መታገድ ለማዘዝ ሰልጣን የተሰጠው ታካሚውን ማየት እና መገምገም አለበት።

(iii) ጠበኛ ያልሆነ እና ራሱን የማይጎዳ ታካሚ አካላዊ ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያገለግል እያንዳንዱ የእገድ ትእዛዝ በሆሰፒታል መመሪያው ፈቃድ እንደነበረው ይታደሳል።

(9) በትእዛዙ ውሰጥ የተገለፀው የጊዜ ርዝመት ምንም ይሁን ምን እገዳው ወይም መነጠል በሚቻልበት ጊዜ መቋረጥ አለባቸው።

(10) የታገደው ወይም የተነጠለው የታካሚው ሁኔታ በሐኪሙ፣ በሆሰፒታሉ ፖሊሲ በተወሰነው የጊዜ ልዩነት ውሰጥ በዚህ ክፍል በአንቀጽ(ረ) የተገለጹትን የሥልጠና መሰፈርቶች ያሟሉ ሀኪም፣ በሌላ ፈቃድ ባላቸው ባለሙያ ወይም የሰለጠኑ ሠራተኞች ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል።

(11) ሀኪም እና ሌሎች ፍቃድ ያላቸው ገለልተኛ ባለሙያ ሰልጠና መሰፈርቶች በሆሰፒታሉ ፖሊሲ ውሰጥ መገለጽ አለባቸው። በትንሹ ሐኪሞች እና ሌሎች ፍቃድ ያላቸው ገለልተኛ ሐኪሞች በሆሰፒታል ፖሊሲ ውሰጥ እገዳ ወይም መነጠል እንዲያዙ የተፈቀደላቸው በግዛቱ ሕግ መሠረት እገዳን ወይም መነጠልን በተመለከተ የሆሰፒታሉ ፖሊሲ የሥራ እውቀት ሊኖረው ይገባል።

(12) የታካሚውን፣ የሰራተኛውን ወይም የሌላኛውን አካላዊ ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል የአመጽ ወይም ራስን የማጥፋት ባህሪ ለማሰተዳደር እገዳ ወይም መነጠል ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ ታካሚው ጣልቃ ገብነት ከተነሳሳ በኋላ በ 1 ሰዓት ውሰጥ ፊት ለፊት መገናኘት አለበት -

(i) በ-

(A) ሐኪም ወይም ሌላ ፍቃድ ያለው ገለልተኛ ባለሙያ፤ ወይም

(B) የተመዘገበ ነርሰ ወይም በዚህ ክፍል በ ኣንቀጽ(ረ) ውሰጥ በተጠቀሰው መሰፈርት መሰረት የሰለጠነ ወይም የሐኪም ረዳት።

(ii) ለመገምገም-

(A) የታካሚው አሰቸኳይ ሁኔታ፤

(B) የታካሚው ለጣልቃ ገብነት የሰጠው ምላሽ፤

(C) የታካሚው የህክምና እና የባህርይ ሁኔታ፤ እና

(D) እገዳውን ወይም መነጠሱን የማሰቀጠል ወይም የማቋረጥ አሰፈላጊነት።

(13) ግዛቶች በዚህ ክፍል በአንቀጽ(ሠ)(12)(i) ላይ ከተዘረዘሩት የበለጠ የሚከለከሉ በሕግ ወይም ደንብ መሰፈርቶችን ለማውጣት ነፃ ናቸው።

(14) በዚህ ክፍል በአንቀጽ(ሠ)(12) የተገለፀው የፊት-ለፊት ግምገማ የሚከናወነው በሰለጠነው ነርሰ ወይም በሐኪም ረዳት ከሆነ የሰለጠነው የተመዘገበ ነርሰ ወይም የሃኪም ረዳት ሀኪሙን ወይም ሌላ ፍቃድ ያለው ገለልተኛ ባለሙያ ማማከር አለበት። የ 1 ሰዓት የፊት-ለፊት ግምገማ ከተጠናቀቀ በኋላ በተቻለ ፍጥነት በ 482.12(ሐ) እንደተጠቀሰው የታካሚውን እንክብካቤ ኃላፊነት ይወሰዳል።

(15) በዚህ አንቀጽ ሰር የተጠቀሱት ሁሉም መሰፈርቶች በተመሳሳይ ጊዜ የእገዳ እና መነጠል ጥቅም ላይ ይውላሉ። በአንድ ጊዜ ገደብ እና መነጠል አጠቃቀም የሚፈቀደው ታካሚው በቀጣይነት ክትትል ከሆነ ብቻ ነው -

(i) በተመደበው የሰለጠነ የሰራተኛ አባል ፊት ለፊት መገናኘት፤ ወይም

(ii) በሰለጠኑ ሰራተኞች ሁለቱንም የቪዲዮ እና የድምጽ መሳሪያዎችን በመጠቀም። ይህ ክትትል ከታካሚ ጋር የቀረበ መሆን አለበት።

(16) እገዳ ወይም መነጠል ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ በሚከተለው የታካሚው የሕክምና መዝገብ ውሰጥ ሰነዶች መኖር አለባቸው፦

(i) እገዳን ወይም መነጠል ዓመፅን ወይም ራስን የማጥፋት ባህሪን ለማሰተዳደር ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ የ1-ሰዓት ፊት ለፊት የሕክምና እና የባህሪ ግምገማ፤

(ii) የታካሚው ባህሪ እና ጥቅም ላይ የዋለው ጣልቃ ገብነት መግለጫ፤ የታካሚው ባህሪ እና ጥቅም ላይ የዋለው ጣልቃ ገብነት መግለጫ፤

(iii) እማራጮች ወይም ሌሎች አነሰተኛ የተገደቡ ጣልቃገብነቶች (እንደአሰፈላጊነቱ)፤

(iv) እገዳው ወይም መነጠል መጠቀምን ያረጋገጠ

የታካሚው ሁኔታ ወይም ምልክት(ቶች)፤ እና

(v) ለተጠቀሙበት ጣልቃ ገብነት(ቶች)ን የታካሚው ምላሽ፣ በተከታታይ ለመጠቀም ምክንያቶችን ጨምሮ።

(f) መደበኛ፦ እገዳን ወይም መነጠል የሰራተኞች ሰልጠና መሰፈርቶች። ታካሚው በሰለጠኑ ሰራተኞች የእገዳ ወይም መነጠል አተገባበር ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን መብት አለው።

(1) የሥልጠና ጊዜዎች። የእግድ አፈፃፀም፣ የመነጠል አተገባበር፣ ክትትል፣ ግምገማ፣ እና በእገታ ወይም እሰር ቤት ውሰጥ ላሉት ታካሚዎች ተገቢውን ብቃት ለማሳየት የሰለጠኑ እና ብቁ መሆን አለባቸው-

(i) በዚህ አንቀጽ ውሰጥ የተጠቀሱትን ማናቸውንም እርምጃዎች ከመፈፀምዎ በፊት፤

(ii) እንደ የመተዋወቂያ አካል፣ እና

(iii) በመቀጠል ከሆሰፒታል ፖሊሲ ጋር ወቅታዊነት በወጥነት።

(2) ሥልጠና ይዘት። ቢያንሰ-ቢያንሰ በሚከተሉት የታካሚውን የህዝብ ፍላጎቶች ላይ በመመርኮዝ ሆሰፒታሉ አግባብነት ያላቸው ሰራተኞች ትምህርት፣ ሰልጠና እና ዕውቀት እንዲኖራቸው ይፈልጋል፦

(i) የእግድ ወይም መነጠል የሚጠይቁ ሁኔታዎችን ሊያሰከትሉ የሚችሉ ሰራተኞች እና የታካሚ ባህሪዎች፣ ክሰተቶች እና አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ለመለየት የሚያሰችሉ ቴክኒኮች።

(ii) አካላዊ ያልሆነ ጣልቃ-ገብነት ችሎታዎች አጠቃቀም።

(iii) በታካሚው የግል ሕክምና፣ ወይም በባህሪ ሁነታ ወይም ሁኔታ ላይ በመመሰረት ዝቅተኛውን ገዳቢ ጣልቃ ገብነት መምረጥ።

(iv) ለአካላዊ እና ሥነ ልቦናዊ ጭንቀት ምልክቶች እንዴት መለየት እና ምላሽ መሰጠት እንዳለባቸው ሥልጠናን ጨምሮ በሆሰፒታሉ ውሰጥ ጥቅም ላይ የዋለው የሁሉም ዓይነት የእግድ ወይም መነጠል ደህንነቱ የተጠበቀ አተገባበር እና አጠቃቀም(ለምሳሌ፣ በሰውነት በአቀማመጥ የሚመጣ የአተነፋፈሰ ችግር)፤

(v) አገዳ ወይም መነጠል ከእንግዲህ አሰፈላጊ እንደማይሆን የሚያመለክቱ የተወሰኑ የባህሪ ለውጦች ክሊኒካዊ መለያ።

(vi) የመተንፈሻ አካልን፣ የዝውውርን ሁነታ፣ እና የደም ዝውውር ሁኔታ፣ የቆዳ አቋም፣ አሰፈላጊ ምልክቶች ጨምሮ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን፣ እና ከ 1 ሰዓት ፊት ለፊት ግምገማ ጋር በተዛመደ የሆሰፒታል መመሪያ የተገለጹ ማናቸውም ልዩ መሰፈርቶች ጨምሮ ውሰን የሆነ ግን የታገደውን ወይም የተነጠለውን ታካሚ አካላዊ እና ሰነ-ልቦናዊ ደህንነትን መቆጣጠር።

(vii) አሰፈላጊውን ወቅታዊ የድጋፍ ማረጋገጫን ጨምሮ የመጀመሪያና እርዳታ ቴክኒኮችን እና ደረትን በመጫን የአተነፋፈሰ/የልብ ሰርዓትን መመለሰ መጠቀምን የምሰክር ወረቀት ይጠይቃል።

(3) የአሠልጣኝ መሰፈርቶች። የሰራተኛ ሰልጠና የሚሰጡ ግለሰቦች በትምህርት ማሰረጃ ያላቸው ሰልጠና፣ እና የታካሚዎችን ባህሪ ለመቅረፍ በተጠቀሙባቸው ቴክኒኮች ውሰጥ ልምምድ ብቁ መሆን አለባቸው።

(4) የሥልጠና ሰነዶች። የሆሰፒታሉ ሰልጠናና የብቃት ማረጋገጫ በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቃቸውን በሆሰፒታሉ የሰራተኞች መዛግብት ውሰጥ ተመዝግበው መያዝ አለባቸው።

(g) መደበኛ፦ የሞት ሪፖርት መሰፈርቶች፦ ሆሰፒታሎች ከመነጠል ወይም የእግድ አጠቃቀም ጋር የተዛመዱትን ሞቶች ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

(1) በዚህ ክፍል አንቀጽ(g)(2) ሰር ከተገለጹት ሞት ልዩ ሁኔታዎች በሰተቀር ሆሰፒታሉ የሚከተሉትን መረጃዎች ለ CMS በየታካሚውን ሞት ካወቀ በኋላ በሚቀጥለው የሥራ ቀን ሳያልቅ፣ ፋክሰ ወይም ኤሌክትሮኒክ በኤሰኤምኤሰ እንደተወሰነው የሚከተለውን መረጃ ሪፖርት ማድረግ አለበት።

(i) ታካሚው በእግድ ወይም በመነጠል ሆኖ እያለ የሚከሰት እያንዳንዱ ሞት።

(ii) ታካሚው ከእግድ ወይም ከተነጠለ ከተለቀቀ በኋላ በ 24 ሰዓታት ውሰጥ የሚከሰት እያንዳንዱ ሞት።

(iii) እገዳው ወይም መነጠል ከገባ በኋላ በ 1 ሳምንት ውሰጥ ለሚከሰት ሆሰፒታል የሚታወቅ እያንዳንዱ ሞት በዚህ ጊዜ በታካሚው ላይ የተገለፀው የእግድ አይነት(ቶች) ምንም ይሁን ምን ታካሚዎቻቸው ላይ የእግድ ወይም ነጥሎ ማሰቀመጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ለታካሚው ሞት አሰተዋጽኦ አድርጓል ብሎ መገመት ምክንያታዊ ነው። በዚህ አውድ ውሰጥ“ለመገመት የሚያመች” የሚለው አባባል ረዘም ላለ ጊዜ የመንቀሳቀስ እገዳን በተመለከተ የተገደሉ ሞቶችን፣ ወይም የደረት መጣበቅ፣ አተነፋፈሰን መገደድን፣ ወይም በኣካላዊ አቀማመጥ ምክንያት መተንፈሰ መቸገርን ያጠቃልላል፣ ግን አይገደብም።

(2) መነጠል ጥቅም ላይ ያልዋለ ከሆነ እና ታካሚው ላይ ብቸኛው እገዳ ሲሰጥ ታካሚው የእጅ አንጓ(ዎች) ላይ ብቻ የተተገበሩ እና ለሰላሳ፣ ግትር፣ ጨርቆች የሚመሰሉ ቁሳቁሶች ብቻ የተገነቡ ናቸው፣ የሆሰፒታሉ ሠራተኞች በውሰጣቸው መዝግብ ውሰጥ ወይም በሌላ ሰርዓት

ውሰጥ መመዝገብ አለባቸው፣ የሚከተለው መረጃ፦

(i) ታካሚው በእንደዚህ ዓይነት እክሎች ውሰጥ በሚሆንበት ጊዜ የሚከሰት ማንኛውም ሞት።

(ii) ታካሚው ከእግድ ወይም ከተነጠለ ከተለቀቀ በኋላ በ 24 ሰዓታት ውሰጥ የሚከሰት እያንዳንዱ ሞት።

(3) ሠራተኞቹ የሞቱበት ቀን እና ሰዓት በታካሚው የሕክምና መዝገብ ውሰጥ ማሰረጃ ማቅረብ አለባቸው።

(i) በዚህ ክፍል አንቀጽ (g)(1) በተገለፀው ሞት ለ CMS ሪፖርት ተደርጓል። ወይም

(ii) በዚህ ክፍል አንቀጽ(g)(2) በተገለፀው ሞት ምክንያት በውሰጣቸው መዝገብ ውሰጥ ወይም በሌላ ሰርዓት ውሰጥ የተመዘገበ።

(4) በዚህ ክፍል በአንቀጽ(ሰ)(2) ለተገለጹት ሞት፣ ወደ ውሰጠኛው መዝገብ ወይም ወደ ሌላ ሰርዓት የሚገቡ ግቤቶች እንደሚከተለው መቅረብ አለባቸው።

(i) እያንዳንዱ ግቤት ታካሚው ከሞተበት ቀን ጀምሮ ከሰባት ቀናት በማይበልጥ መሆን አለበት።

(ii) እያንዳንዱ ግቤት በታካሚው § 482.12(ሐ)፣ በሕክምና መዝገብ ቁጥር እና በዋነኝነት ምርመራው ላይ በተጠቀሰው መሠረት የታካሚውን ሰም፣ የትውልድ ቀን፣ የሞተበት ቀን፣ የሚከታተል ሐኪም ወይም ሌላ ፈቃድ ያለው ገለልተኛ ባለሙያ መመዝገብ አለበት።

(iii) ከተጠየቀ በኋላ መረጃው በጽሑፍም ሆነ በኤሌክትሮኒክ መልክ ለ CMS ወዲያውኑ መቅረብ አለበት።

(h) መደበኛ፦ የታካሚ ጉብኝት መብቶች። ሆሰፒታል በእንደዚህ ያሉ መብቶች ላይ እና ክሊኒካዊ ገደቡ ወይም ገደቡ ላይ የሚያሰፈልጉትን ማንኛውንም ክሊኒካዊ አሰፈላጊ ወይም ምክንያታዊ ገደቦችን የሚያሰቀምጡትን ጨምሮ ሆሰፒታሎች የታካሚዎችን የመጎብኘት መብትን የሚመለከቱ የጽሑፍ ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች ሊኖሩት ይገባል። አንድ ሆሰፒታል የሚከተሉትን መሰፈርቶች ማሟላት አለበት፦

(1) እያንዳንዱን ታካሚ (ወይም ድጋፍ ሰጪ ግለሰብ፣ አሰፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ) ክሊኒካዊ ገደቦችን ወይም ወሰኖችን ጨምሮ በዚህ ክፍል ውሰጥ ያለውን ሌሎች መብቶች እንዲያውቅ ሲደረግ እያንዳንዱን ታካሚ ጨምሮ የእርሱን ወይም የእርሷን የጉብኝት መብቶች ማሳወቅ።

(2) የትዳር ጓደኛን፣ የቤት ውሰጥ አጋር(ተመሳሳይ የሆነን ጨምሮ) ጨምሮ እርሱ የሰየመውን ጎብኝዎች ለመቀበል በእነሱ ወይም በእሷ ፈቃድ መሠረት ለእያንዳንዱ ታካሚ (ወይም ድጋፍ ሰጪ ግለሰብ፣ አሰፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ) ማሳወቅ ተመሳሳይ ጾታ የቤት ውሰጥ አጋር)፣ ሌላ የቤተሰብ አባል፣ ወይም ጓደኛ፣ ይህን በማንኛውም ጊዜ ፈቃድ የማንሳት ወይም የመከልከል መብት አለው።

(3) በቀለም፣የሀገርን፣የሃይማኖትን፣ የጾታ ማንነትን፣ የጾታ ዝንባሌ ወይም የአካል ጉዳትን መሠረት በማድረግ የጎብኝዎች መብቶችን አይገድቡ፣ አይወሰኑ ወይም አይከለክሉ።

(4) ሁሉም የጎብኝዎች ከታካሚዎች ምርጫዎች ጋር በሚሰማማ መልኩ ሙሉ እና እኩል የጎብኝዎች ልዩ መብቶች ማግኘታቸውን ያረጋግጡ።

[71 FR 71426, ዲሴምበር 8, 2006, ተሻሻለ በ 75 FR 70844, ኖቬምበር 19, 2010፤ 77 FR 29074, ሜይ 16, 2012]

እንደ ታካሚ ያሉብዎት ኃላፊነቶች

በእኛ ተቋማት ውሰጥ እንደ እንደ ታካሚ እያሉ በጣም የተቻለውን ምርጥ ተሞክሮ እንዳለዎት ማረጋገጥ እንፈልጋለን። እነዚህን ኃላፊነቶች በመወጣት ሊረዱ ይችላሉ።

- **በተቻለዎት መጠን ከጤናዎ ጋር በተዛመደ ትክክለኛ እና የተሟላ መረጃ መሰጠት።**
- **የሕክምና ቡድንዎን ማወቅ እና በሁኔታዎ ላይ ሰላለ ማንኛውም ለውጥ መንገር።**
- **በጤናዎ እንክብካቤ ውሰጥ መሳተፍ እና የህክምና እቅድዎን መከተል።**
- **መመሪያዎችን እና እካሄዶችን የማይረዱ ከሆነ ወይም እነሱን መከተል እንደማይችሉ ሆኖ ከተሰማዎት ጥያቄዎችን መጠየቅ።**
- **የደህንነት ህጎችን እና ፖሊሲዎችን በመጠበቅ ከሆሰፒታል ሰራተኞች ጋር መተባበር።**
- **ጫጫታዎችን እና የጎብኝዎችን ቁጥር በመገደብ ለሌሎች ታካሚዎች አሳቢ ለመሆን።**
- **እርሰዎን የሚንከባከቡዎትን የሆሰፒታሎች ሰራተኛ አሳቢ መሆን እና የሆሰፒታል ንብረት ማክበር።**
- **የመልቀቂያ ዕቅዶችን በኃላፊነት እና ወቅታዊ በሆነ ሁኔታ ለማከናወን ማገዝ።**
- **ለተቀበሉት አገልግሎቶች ክፍያ ለማመቻቸት መተባበር።**
- **ቀጠሮዎችን መጠበቅ እና መድሃኒቶችዎን ማወቅ።**

መብቶችዎን ወይም የሕክምና እንክብካቤዎን በተመለከተ ጥያቄ ካለዎት ከሚከተሉት ተቋማት ውስጥ አንዱን ያነጋግሩ፦

M Health Fairview Patient Relations
1690 University Ave. W, Minneapolis, MN 55104
612-672-1000
patientrelations@fairview.org

University of Minnesota Physicians Patient Relations
M Health Fairview Clinics and Surgery Centers
720 Washington Ave. SE, Suite 200,
Minneapolis, MN 55414
612-884-0661
cscfeedback@mhealth.org

Fairview Range Medical Center
750 34th St. E, Hibbing, MN 55746
218-362-6656 ፋክስ: 218-362-6619

Grand Itasca Clinic and Hospital
1601 Golf Course Road
Grand Rapids, MN 55744
218-360-4212

መብቶችዎን ወይም የሕክምና እንክብካቤዎን በተመለከተ ጥያቄ ካለዎት ያነጋግሩ፦

Minnesota Board of Medical Practice
2829 University Ave. S.E., Suite 500
Minneapolis, MN 55414-3246
612-617-2130 ወይም 800-657-3709

Office of Health Facility Complaints
P.O. Box 64970, St. Paul, MN 55101-0970
651-201-4201 ወይም 800-369-7994

Office of Quality and Safety Monitoring
የታካሚ ደህንነት ክስተት ወይም ስለጤና እንክብካቤ ድርጅት አሳሳቢነት ሪፖርት ለማድረግ።.
ኦንላይ፦ ቅጽ ይሙሉ በ www.jointcommission.org
ፋክስ፦ 630-792-5636
ደብዳቤ፦ The Joint Commission
One Renaissance Blvd., Oakbrook Terrace, IL 60181

Office of Ombudsman for Mental Health and Development Disabilities
121 East 7th Place, Suite 420, St. Paul, MN 55101-2117
651-757-1800 ወይም 1-800-657-3506

Minnesota Board of Behavioral Health and Therapy
2829 University Avenue SE, Suite 210, Minneapolis, MN 55414
612-548-2177

Minnesota Department of Human Services-Licensing Division
P.O. Box 64242, St. Paul, MN 55164-0242
651-431-6500 ወይም 6500-6500-6500

ስለ Medicare መብቶችዎ የሚያሳስቧቸው ነገሮች፣ የእንክብካቤ ጥራት ወይም ያለጊዜው መቋረጥን ጨምሮ፣ ያነጋግሩ፦

Office of Ombudsman for Long-Term Care
P.O. Box 64971, St. Paul, MN 55164-0971
651-431-2555 ወይም 800-657-3591

Medicare Quality Improvement Organization(QIO)
Livanta- BFCC QIO
10820 Guilford Road, Suite 202
Annapolis Junction, MD 20701-1262
1-888-524-9900 ወይም TTY 1-888-985-8775
www.livantaqio.com